# የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር

## የስፖርት ውርርድ ሎተሪ መመሪያ
## ቁጥር 140/2013

ጥቅምት 2005 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

## የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 140/2013

በአገራችን የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች መዘውተር ከጀመረ ቆየት ያለ ሲሆን በተጨማሪ በአገሪቱ በሰፊው እየተስተዋለ ካለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር በተያያዘ በስፖርቱም ዘርፍ ከፍተኛ የሆነ መነቃቃት እየታየ በመሆኑ፤

ዘመኑ ባፈራው በዲኤስቲቪ/dstv/ የሚተላለፉ የአውሮፖ የእግር ኳስ ውድድሮች በይበልጥ ለወጣቱ እንደዋነኛ የጊዜ ማሳለፊያና መዝናኛ በመሆን እያገለገለ የሚገኝ በመሆኑ ስፖርታዊ ውድድሮችን መሠረት ያደረጉ የዕድል ሙከራ ጨዋታዎች በስፋት እየተዘወተሩ መምጣታቸውና ህብረተሰቡም በእነዚህ የዕድል ጨዋታዎች ለመሳተፍ ያለው ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ በዘርፉ ፈቃድ አውጥተው ለመሰማራት የሚፈልጉ ግለሰቦች/ድርጅቶች ጥያቄ እየተበራከተ በመምጣቱ እና በደንብ ቁጥር 160/2001 አንቅጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ በማውጣት ሲያካሄዱ እንደሚችሉ በመደንገጉ፤

ሥራውን በህግ አግባብ የበለጠ ግልጽና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለመምራት ተገቢ በመሆኑ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደርን እንደገና ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሎተሪ ሥራን የማካሄድ፣ የማስተዳደርና የመቆጣጠር እንዲሁም በሕግና በስርዓት እንዲመራ የማድረግ ስልጣን ለአስተዳደሩ በመስጠቱ ከላይ በተጠቀሰው ደንብ ቁጥር አንቀፅ 21 መሠረት ደንቡን ለማስፈጸም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ይህን የስፖርት ውርርድ ሎተሪ መመሪያ አውጥቷል።

### አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የስፖርት ውርርድ ሎተሪ መመሪያ ቁጥር 140/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

*አንቀጽ 2 ትርጓሜ*

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር፡-

1. “ባለስልጣን” እና ”ዋና ዳይሬክተር” ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ዋና ዳይሬክተር ነው፣
2. “አስተዳዳር” ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ነው፣
3. “የአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊ” ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር እና ም/ዋና ዳይሬክተር ናቸው፡፡
4. “የስፖርት ውርርድ ሎተሪ” ማለት በቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ የሚከናወኑ የስፖርት ውድድሮችን መሠረት በማድረግ የሚደረግ ውርርድና ሽልማቱ በገንዘብ ወይም በዓይነት የሚሰጥ የሎተሪ ዓይነት ነው፣
5. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
6. “ፈቃድ” ማለት ትንበያን ወይም ዕድልን መሠረት ያደረገ የስፖርት ውድድር የውርርድ ሎተሪ በማካሄድ ከጨዋታው የሚገኘውን የተጣራ ገቢ ሙሉ በሙሉ ወይም ከተጣራ ገቢያቸው 20% እና ከዚያ በላይ የሚሆነውን ለማህበራዊ አገልግሎት ማለትም ለስፖርት ተቋማት፣ ለስፖርት ቡድኖች... ወዘተ ለመስጠት በጹሁፍ በሚገቡት ውል መሠረት ለሚስማሙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
7. “ክፍያ” ማለት በአስተዳደሩ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 አንቀጽ 18 መሠረት የሚፈጸም የአዲስ ፈቃድ ማውጫና፣ በአንቀጽ 19(1) (ሀ) መሠረት ከስፖርት ሎተሪ ትኬት ሽያጭ ሊገኝ ይችላል ተብሎ በሚገመተው ጠቅላላ ገቢ ላይ ተሰልቶ የሚፈጸም የ15% ኮሚሽን ክፍያ ነው፣
8. “ደንብ” ማለት የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 ነው፡፡
9. “ውል” ማለት በፈቃድ ሰጪውና ተቀባዩ መሐል በተሰጠው የፈቃድ አካሄድ ላይ የሚደረስ ስምምነት ነው፡፡
10. “አዋጅ” ማለት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 ነው፡፡

11. "ገቢ. ሰብሳቢ. መስሪያ ቤት" ማለት በዚህ መመሪያ የገቢ. ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 33 መሠረት ከዕድል ጨዋታ የሚገኝ ገቢ. ተቀባይ ነው፡፡
12. "የአስተዳደሩ ኢንስፔክተሮች" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ ያወጡ ግለሰቦችን/ድርጅቶች የዕድል ጨዋታው አካሄድ በመመሪያው መሠረት እየተካሄደ መሆኑን የሚከታተሉና የሚቆጣጠሩ ናቸው፡፡
13. "ለአንድ ጨዋታ" ማለት በሁለት ቡድኖች መካከል የሚካሄድን አንድ ጨዋታን መሠረት አድርጎ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
14. "ሙሉ የጨዋታ ወቅት" ማለት እንደ ስፖርት ዓይነቱ ውድድሩ ተጀምሮ እስከሚያልቅ ድረስ ረዥም ጊዜ የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንኑ መሠረት አድርጎ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡
15. "ከሚገኘው ጠቅላላ ገቢ" ማለት በስፖርት ውድድር ውርርድ ከሚሳተፉ ተወራራጆች የሚገኘውን ገቢ. የሚያመለክት ነው፡፡
16. "የተጣራ ገቢ." ማለት የስፖርት ውድድር ውርርድ የሚያካሄደው ሰው ለውርርዱ አሸናፊዎች የሚያወጣውን ወጪ. እና ሌሎች ስራውን ለመስራት የሚያስችሉትን ቀጥተኛ ወጪዎች ቀንሶ ከስፖርት ውርርዱ የሚያገኘው የተጣራ ገቢ. ነው፡፡
17. "ቋሚ ፈቃድ" ማለት በዓመቱ እየታደሰ በዘላቂነት ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል ፈቃድ ነው፡፡
18. "ጊዜያዊ ፈቃድ" ማለት ለአንድ ጨዋታ ወይም በአንድ ወቅት የሚካሄዱ ጨዋታዎችን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

አንቀጽ 3 <u>ፈቃድን በተመለከተ</u>

*የፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ ሁኔታ*

ሀ. ማንኛውም ሰው የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ለማካሄድ ሲፈልግ ውድድሩ ከመካሄዱ ከሰባት /7/ ተከታታይ ቀናት በፊት ለአስተዳደሩ በጽሁፍ የፈቃድ ጥያቄውን በማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ. ፈቃድ ጠያቂ ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር የሚከተሉትን መረጃዎች አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

1. የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ ጠያቂውን ስምና ሙሉ አድራሻ፣

2. የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ ለማካሄድ ፈቃድ የሚጠይቅበት የስፖርት ዓይነት፣ የስፖርታዊ ውድድሩ ስያሜ፣ የስፖርት ውድድሩ መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚያበቃ፣ የተቃራኒ/የተፋላሚ ቡድኖች የግጥሚያ ድልድል፣ የት ክልል እና ቦታ እንደሚካሄድ፣ በስንት ሰዓት እንደሚካሄድ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎችን፣

3. ስፖርታዊ ውድድሩ በሚካሄድበት ቦታ በመገኘት የስፖርት ውድድር የውርርድ ሎተሪውን ለማካሄድ የስፖርት ጨዋታውን ከሚያዘጋጀው ድርጅት የተገኘ ፈቃድና ምቹ ቦታ ስለመኖሩ የሚገልጽ ማስረጃ፣

4. የስፖርት ጨዋታው እንዳለቀ የውርርድ አሸናፊዎችን ለመለየት የሚያስችል የዕጣ ማውጫ ዘዴ፤ እንደ ኮምፒዩተር ያለ የዕጣ ማውጫ ሶፍት-ዌር መጠቀም ያለመጠቀሙን መግለጽ፣

5. ለውርርድ ጨዋታው አሸናፊዎች የሚሰጣቸው ሽልማቶች በዓይነት የሚሰጡ ከሆነ ለሽልማት የተዘጋጀውን ዕቃ/ንብረት መለያ ስም/ብራንድ/፣ ዕቃው የተመረተበትን አገር፣ የሽልማቱን ብዛት፣ የእያንዳንዱን ዕቃ/ንብረት ዋጋ፣ ለገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ ማድረግ የሚገባው ከሽልማቱ ላይ የሚሰበሰብ የገቢ ግብር እና ለሽልማት የተዘጋጁትን ዕቃዎች/ንብረቶች ጠቅላላ ዋጋ፣

6. ለሽልማት የሚቀርቡት ዕቃዎች በግዥ ወይም በስጦታ በህጋዊ መንገድ የተገኙ ስለመሆናቸው የሚገልጽ ማስረጃ፣

7. በስፖርት ውርርድ ሎተሪ የሚሳተፈው ተወራራጅ የሚከፍለው ፣ በእያንዳንዱ ጨዋታ የተሳታፊው ብዛት እና ጠቅላላ ገቢ ግምት፤

8. ስፖርታዊ ጨዋታው እንደተጠናቀቀ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ አሸናፊዎችን በመለየት አሸናፊውን ለተሳታፊው/ለታዳሚው/ የሚገለጽበትን መንገድ የሚያሳይ ማስረጃ፣

9. የጨዋታው አሸናፊ እንዴትና በምን ሁኔታ እንደሚለይ የሚገልጽ ሰፋ ያለ ማብራሪያ፣ እና

10. ሌሎች ፈቃድ ለማግኘት ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ማናቸውንም ተጨማሪ መረጃዎች፤

ግብሩን ለገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ ያደረገበትን ማስረጃ ክፍያው በተፈፀመ በማግስቱ ለአስተዳደሩ ማቅረብ አለበት፣

10. በስፖርታዊ ውርርድ ሎተሪው ላይ ከሚሳተፉት መካከል ብዙ አሸናፊዎች የሚኖሩ ከሆነ ለሽልማቱ የተመደበው የዓይነት/ገንዘብ ሽልማት ለአሸናፊዎቹ እንደየ ድርሻቸው የሚካፈልበትን ሁኔታ በቅድሚያ የማዘጋጀት ግዴታ አለበት፤
11. በስፖርታዊ ውርርድ ሎተሪ የሚካሄድበት ጨዋታ በተባለው ሰዓት ባይካሄድ፣ በኤሌክትሪክ መቋረጥ ጨዋታው ባይታይ ውጤቱ ቢሰረዝ ወይም የጨዋታው ዓይነት ቢለወጥ በውርርዱ ተሳታፊ ለሆኑት በትኬታቸው መሠረት የተወራረዱበትን ገንዘብ በመሉ ተመላሽ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤
12. አጠቃላይ እንቅስቃሴው በሂደት ላይ እያለም ሆነ ከተጠናቀቀ በኂላ እንደአስፈላጊነቱ በአስተዳደሩ ቁጥጥር የሚደረግ ሲሆን ባለፈቃዱ ከትኬት ህትመት፣ ሥርጭት፣ ሽያጭ፣ ዕጣ ክፍያ ወዘተ ጋር የተያያዙ የሂሳብ ሰነዶችን በጥንቃቄ መያዝ እና ከሁለት ዓመት ላላነሰ ጊዜ እንዲቀመጥ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤
13. የስፖርት ውርርድ ሎተሪ በሚካሄድበት ቦታ ማንኛውንም ሌሎች የዕድል ሙከራ ጨዋታዎችን እንዳይካሄድ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤

*አንቀጽ 5. <u>ፈቃድ ስለሚከለከልበት ሁኔታ</u>*

*የፈቃድ ይሰጠኝ ጥያቄ፡-*

1. አስተዳደሩ የቀረበለት የፈቃድ ጥያቄ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 በፊደል (ለ) ስር በተገለጹት ዝርዝር መረጃዎችና ማስረጃዎች ካልተደገፈ፣ እና
2. ፈቃድ ጠያቂው በቅድሚያ ለአስተዳደሩ የፈቃድ ማውጫ ክፍያ ከፍሎ ከስፖርት ውርርድ ሎተሪ ከሚገኘው አጠቃላይ ገቢ ላይ 15% ኮሚሽን ክፍያውን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ተራ ቁጥር (1) እና (2) ሥር በተቀመጠው መሠረት በተገለፀው የጊዜ ገደብ ካልከፈለ ለቀጣይ ሥራው ፈቃድ አይሰጠውም።

## አንቀጽ 6. ፈቃድን ስለማገድ ወይም ስለመሰረዝ

ማንኛውም የስፖርት ውርርድ ሎተሪ እንዲያካሂድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፈቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡-

1. ፈቃድ የሚያሳግዱ ሁኔታዎች

ሀ. ፈቃድ ወሳጁ በተሰጠው ፈቃድ ከአስተዳደሩ ጋር ከፈጸመው ውል ውጭ ሲሰራ ከተገኘ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚታዩበትን ጉድለቶች በማስመልከት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ፡-

1. መጀመሪያ የቃል ማስጠንቀቂያ፣
2. የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ተደርጎ የማስተካከያ ሥራ ካልሰራ፣
3. የማገድ እርምጃ ይወሰዳል፣

ለ. የስፖርት ውርርድ ሎተሪውን አካሄድ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ለተሰማሩ የአስተዳደሩ ኢንስፔክተሮች መረጃ እና ማስረጃ በመስጠት ለመተባበር ፍቃደኛ ካልሆነ፤

ሐ. በሥራው ላይ ፍርድ ቤት የእገዳ ትዕዛዝ ከሰጠ እግዱ እስከሚነሳ ወይም በጉዳዩ ላይ ዘላቂ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ታግዶ ሊቆይ ይችላል፤

2. ፈቃድ የሚያሠርዙ ሁኔታዎች

ሀ. ፈቃድ የተሰጠው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ለ. አስተዳደሩ ሳይፈቅድ የተሰጠውን ፈቃድ ለሦስተኛ ወገን በማንኛውም መንገድ አሳልፎ ከሰጠ፤

ሐ. በተሰጠው ፈቃድ ላይ ሥራውን ሳይጀምር ለሁለት ወር /60 ቀናት/ ያህል ጊዜ ከቆየ፤

3. የፈቃድ መታገድና መሰረዝ ሁኔታ

ሀ. ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው ከአስተዳደሩ የጽሁፍ ማስታወቂያ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ የተሰጠውን ፈቃድ በ7/ሰባት/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ለአስተዳደሩ የመመለስ ግዴታ አለበት።

ለ. ፈቃድ ስለመታገዱ ወይም ስለመሰረዙ ለአስተዳደሩ ማስታወቂያው በደረሰው 15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለአስተዳደሩ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል።

*አንቀጽ 7 የፈቃድ ማውጫ እና ዕድሳት ክፍያ*

ማንኛውም የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ ጠያቂ ሰው ለተሰጠው የፈቃድ መስጠት አገልግሎት የብር 400.00 /አራት መቶ ብር/ ክፍያ፣ የፈቃድ ዕድሳት ለማድረግ ከሆነ የብር 200.00 /ሁለት መቶ/ ክፍያ ይፈጽማል፣

*አንቀጽ 8 የኮሚሽን ክፍያ*

ፈቃድ ጠያቂው ሰው ከስፖርታዊ ውርርድ ሎተሪ ትኬት ሽያጭ ከሚገኘው ጠቅላላ ገቢ ላይ 15% ተሰልቶ ለአስተዳደሩ የኮሚሽን ክፍያ መፈጸም ያለበት ሲሆን አፈፃፀሙ:-

1. ለአንድ ጨዋታ ፈቃድ ወስዶ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ለሚያካሂድ ሰው ጨዋታው እንዳለቀ ባሉት 15 /አስራ አምስት/ ተከታታይ ቀናት ውስጥ፣
2. ለሙሉ የጨዋታ ወቅት ፈቃድ ለሚወስዱ ደግሞ በየወሩ ወር በገባ እስከ አስራ አምስተኛው ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ለአስተዳደሩ ኮሚሽን መክፈል አለበት።

*አንቀጽ 9. የገቢ ግብር አከፋፈል*

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 33 መሠረት ከብር 100.00 (አንድ መቶ) በላይ ለሆነው የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ጨዋታ ለአሸናፊ ከሚሰጥ ሽልማት ላይ 15% የገቢ ግብር በባለፈቃዱ አማካይነት ተሰብስቦ ለግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ መደረግ አለበት። አፈፃፀሙም:-

1. ከብር 100.00 (አንድ መቶ) በላይ ለሆነው የገንዘብ ሽልማት 15% የገቢ ግብር የሚቆረጠው ከዕድለኛው ላይ ሲሆን፣
2. ከብር 100.00 (አንድ መቶ) በላይ ለሚያስገኙ የዓይነት ሽልማቶች 15% የገቢ ግብር በስፖርት ውርርድ ሎተሪ አዘጋጁ ይከፈላል።

አንቀጽ 10 የክፍያ ግዴታን አዘግይቶ በመክፈል የሚጣል አስተዳደራዊ መቀጫ

ማንኛውም የስፖርት ውርርድ ሎተሪን ለማካሄድ ፈቃድ የወሰደ ሰው በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለአስተዳደሩ የሚጠበቅበትን ክፍያ ያልከፈለ እንደሆነ የሚከተለውን አስተዳደራዊ መቀጫ እንዲፈፀምበት ይደረጋል፣

1. ለነጠላ ጨዋታዎች ፈቃድ ለወሰዱ ጨዋታው እንዳለቀ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለሙሉ ሲዝን(የጨዋታ ወቅት) ፈቃድ የወሰዱ ደግሞ ወር በገባ ባሉት 15 /አስራ አምስት/ ተከታታይ ቀናት ውስጥ መፈጸም የሚገባቸውን ክፍያ ሳይፈጸሙ የተጠቀሰው ቀን ካለፈ እና እስከ ቀጣዩ 15 ቀን ከከፈለ የክፍያውን 20% መቀጫ ጨምሮ ይከፍላል።
2. ለሙሉ ሲዝን ጨዋታ ክፍያው ለ2 /ለሁለት/ ተከታታይ ወራት ሳይፈጸም ከቀረ የሁለቱን ወራት ክፍያ 50% መቀጫን ጨምሮ ይከፍላል፤
3. ክፍያው ከሁለት ተከታታይ ወራት በላይ ከዘገየ ከ100% መቀጫ ጋር እንዲፈጸም ሆኖ ፈቃዱ እንዲሰረዝ ይደረጋል።

አንቀጽ 11. የትኬት መሸጫ ሰዓትን ስለመወሰን

የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ለማካሄድ የትኬት ሽያጭ የሚጀመረው ጨዋታውን ለመመልከት ለመጡት የጨዋታው ታዳሚዎች ብቻ ጨዋታው እስከሚጀመር የሚሸጥ ሲሆን የትኬት ሽያጩ ጨዋታው ከመጀመሩ 5 ደቂቃ በፊት ይቆማል።

አንቀጽ 12 ስለ ጨዋታው ተሳታፊዎች

ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ሰው በጨዋታው መሳተፍ ይችላል።

አንቀጽ 13 የተከለከሉ ጉዳዮች

1. የስፖርት ውርርድ ሎተሪን በሚካሄድበት ቦታ የሚሠሩ ሠራተኞች የስፖርት ውርርድ ሎተሪ እንዲጫወቱ አይፈቀድም፤
2. ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው የስፖርት ውርርድ ሎተሪ እንዲጫወት አይፈቀድለትም፤

3. የስፖርት ውርርድ ሎተሪ በሚካሄድበት ቦታ ማናቸውንም ሌሎች የዕድል ሙከራ ጨዋታዎች ማካሄድ የተከለከለ ነው፡፡

*አንቀጽ 14* ***<u>ፈቃድ ማውጣት የሚችሉትን ሰዎች ስለመወሰን፣</u>***

ከስፖርት ውርርድ ሎተሪ የሚገኘውን የተጣራ ገቢ ሙሉ በሙሉ የጋራ ማህበራዊ ዓላማን ለማስፈፀም ማለትም ለስፖርት ክለብ/ቡድን፣ ለስፖርት ፌዴሬሽን፣ ለበጎ አድራጎት ሥራ፣ ለልማት ሥራ ወይም የተጣራ ገቢውን 20% ለጋራ ማህበራዊ ዓላማ ወይም በጎ ተግባር ለማዋል የሚስማማና ለዚህም ማስረጃ ማቅረብ የሚችል ማንኛውም ሰው የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ለማካሄድ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

*አንቀጽ 15* ***<u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>***

1. አስተዳደሩ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡ/የተመለከቱ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
2. የአስተዳደሩ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ የተሰጠውን የሥልጣን ማረጋገጫና መታወቂያ ወረቀት ቁጥጥሩ ለሚካሄድበት ድርጅት ባለቤት፣ ወኪል፣ አጫዋች ሠራተኞች በማሳየት በማናቸውም ጨዋታው በሚካሄድበት ቦታና ሰዓት ቁጥጥር ያደርጋል፣

*አንቀጽ 16 የ<u>ፈቃድ ዕድሳትን በተመለከተ</u>*

የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ፈቃድ የሚያገለግለው በዝርዝር ተጠቅሰው ፈቃድ ለተጠየቀባቸው የጨዋታ ዓይነቶች ወይም ደግሞ ለአንድ ወቅት በቡድኖች መካከል ለሚደረግ ጨዋታ ብቻ ሲሆን ቋሚ የሥራ ፈቃዱ በየዓመቱ ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ነሐሴ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

*አንቀጽ 17 <u>ስለ ቅጣት</u>*

ንኛውም ሰው ያለፈቃድ የስፖርት ውርርድ ሎተሪ ዝግጅት ካካሄደ የአስተዳደሩን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 160/2001 መሠረት አድርጎ እንደጥፋቱ አይነት የሚወሰነው ቅጣት ተፈፃሚ ይደረግበታል፡፡

አንቀጽ 18 <u>መመሪያው ሥራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

አዲስ አበባ................ቀን 2005 ዓ.ም

መላኩ ፋንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
ዋና ዳይሬክተር